## የኮሮና ቫይረስ ስርጭትና ልጆችን የማረጋጊያ ዘዴዎች።

የኮሮና ቫይረስ በእስራኤል ይሰራጫል ተብሎ በመገመቱ ምክንያት በተወሰኑ ቦታዎች ተማሪዎች ት/ቤት እንዳሄዱና ከቤታቸው እንዳይወጡ ትዕዛዝ በመተላለፉ ምክንያት የእናንተ የወላጆች ሀላፊነት እነሱን ለማረጋጋት ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳላችሁ እንድትገነዘቡ እንገልፃለን።

እናንተ ወላጆች ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በትክክልና በእርጋታ መንፈስ ለልጆቻችሁ በማስተላለፍ ሀላፊነታችሁን እንድትዋጡ በጥብቅ እናሳስባለን።

<u>መውሰድ ከሚገባችሁ እርምጃዎች አንዳንዶቹ እንደሚከተለው ይሆናሉ።</u>

1. ችግሩን ለመቋቋም ሀይልና ችሎታ እንዳላችሁ እንደቤተሰብም እንዲሁም ልጆቻችሁ ጠንካራ እንደሆኑ ማስረዳትና ማሳመን አለባችሁ።
2. ለልጆቻችሁ የምታስተላልፉት መልክት አጭርና ከእድሜቸው ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለመት።
3. ልጆች የቀን ቀን እንቅስቃሴቸውን መቀያየር ስለማይወዱ በዚህ ወቅትና ችግር ምክንያት የሚደረጉት ለውጥ ሁሉ መጠኑን እንዳያልፍ መጠንቀቅ አለባችሁ።
4. በአለነበት ዘመን በተለይ በልጆች ዘንድ ሚድያ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫዎት ከሁኔታውና ከእድሜቸው ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል።
5. ለማንኛውም ነገሮችን ለማቃለል ምን ማድረግ እንደሚቻል ከልጆች ጋር መነጋገርና መወያየት አስፈላጊ ነው።

ይሁን እንጅ ከፍተኛ ችግር ከተፈጠረና በተለይ ያለመረጋጋት ፀባይ በልጆች ዙሪያ ከተከሰተ በአስቸኳይ ወደ ባለ ሙያ በመሄድ ምክር መቀበል እንዳለባችሁ እናሳስባለን።

ለማንኛውም ዘወትር 8:00 ከጥዋቱ እስከ 19:00 ከምሽቱ ባለሙያዎች ከዚህ ቦታች በተጠቀሰው ስልክ ቁጥር በመደወል ማነጋገር ይቻላል።

1-800-25-0025

073-3931111

ከአክብሮት ጋር

የሳይኮሎጅ አገልግሎት አስተዳዳሪ ክፍል

በትምህርት ሚኒስተር መ/ቤ ት